**የኢ/ከ/የት/መ 01/2017**
**አንደኛ ዕትም**
**22/01/2017**

# የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የአሰራርና የአደረጃጀት መልካም ተሞክሮ ሰነድ




**መስከረም 2017 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

# የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የአሰራርና የአደረጃጀት መልካም ተሞክሮ ሰነድ

**የመጀመሪያ ዕትም ጥቅምት 2017 ዓ.ም**

መስከረም 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

©መብቱ በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የተጠበቀ ነው፡፡

መስከረም 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የዋና ዳሬክተሩ መልዕክት




የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ሀገራችን ውስጥ በሚገኙ ከተሞች በጎ ፈቃድ አማካኝነት በ2001 ዓ.ም የተመሠረተና ተጠያቂነቱም ለአባላቱ የሆነ ፤ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግሰታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡ድርጅታችን አሁን ላይ ከ98 በላይ ከተሞችን በአባልነት አቅፎ የያዘ ሲሆን ከተሜነትን በማስፋፋትና የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት የበኩልን አሰተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

ተቋማችን ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የከተማ ልማት ዘርፍን በሚመለከት የመማማሪያ፣ የእውቀት ሽግግርና የመግባቢያ መድረክ በመሆን በአባል ከተሞች ውስጥ በተለያዩ እርከን የሚገኙ አስተዳደሮች ተልዕኳቸው በብቃት ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተሳካ እንዲሆን በማገዝ ላይ ይገኛል፡፡

ይህም ሆኖ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ላለፉት ዓመታት በርካታ ውጣ ውረዶችንም ያሳለፈ ቢሆንም ካለፉት 4 ዓመት ወዲህ ግን ማህበሩ ባደረገው መሰረታዊ የመዋቅር ለውጥ በርካታ አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡

በተለይም ለአባል ከተሞች እየሰጣቸው የሚገኙ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ጥራታቸውን የጠበቁ አገልግሎቶች የማህበሩን ገጽታ፣ ክብርና ዝና የበለጠ እንዲጎለብት መንገድ ጠርገውለታል፡፡ ይህንኑም ተግባር በማጠናከር በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀትና የእውቀት ሽግግር በማድረግና አንዱ ከተማ ከሌላኛው ትምህርት እንዲቀስም መድረክ በማመቻቸት በከተማ ልማት ዘርፍ እድገት ዙሪያ የራሱን አሻራ በማሳረፍ ላይ ይገኛል፡፡ በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይገደብ የውጪ ሃገራትን ተሞክሮዎች በመቀመርና የጉብኝት ፕሮግራም በማዘጋጀት አባል ከተሞቹ የተሻለ ልምድ እንዲያገኙ መንገድ አመቻችቷል፤ ወደፊትም ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በዚህና በተከታታይ በምናቀርብላችሁ የተሞክሮ ሰነዶች ላይ የድርጅታችን አባል ከተማ ከንቲባዎችና የማኔጅመንት አባላት ከግንቦት 26-30 2016 ዓ.ም በኔዘርላንድ አገር ያደረጉትን ትምህርታዊ ጉብኝት እንዳስሳለን፡፡ እናም በዚህ ትምህርታዊ ጉብኝት በተመረጡ የኔዘርላንድ ከተሞች በከተማ ልማት ዘርፍ የተከናወኑ በርካታ ቁምነገሮች ለአባል ከተሞቻችን ምርጥ ተሞክሮ ይሆናሉ ብለን በማሰብ የተለያዩ የተሞክሮ ሰነዶችን አዘጋጅተናል፡፡ በዚህ ሰነድ የትብብር መድረኩ መሰል ተቋም የሆነው የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG) የአሰራርና የአደረጃጀት ተሞክሮ የቀረበ ሲሆን የተለያዩ ልምዶችን የምትቀስሙበት በመሆኑ እንደታነቡት ስጋብዛችሁ በደስታ ነው፡፡

መልካም ንባብ!!

**አቶ አንዱአለም ጤናው ሃብቴ**
**የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ዋና ዳይሬክተር**

**ማውጫ**


መግቢያ ..... 6

1. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG) ምስረታ ታሪክ ..... 7

2. ስለ ኔዘርላንድ ከተሞች አጭር መረጃ ..... 9

3. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባልነት ..... 9

4. ያልተማከለ አስተዳደር በኔዘርላንድ (Tradition of local democracy and decentralization) ..... 12

5. የጥብቅና እና የአባል ከተሞች ድምጽ (Advocacy and Voice) ..... 13

7. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የልምድ ልውውጥ መድረኮች (VNG- Platform) ..... 16

8. የአባል ከተሞች ተሳትፎ ..... 27

9. ተቋማዊ አደረጃጀት ..... 30

10. አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG- International) ..... 35

11. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ..... 36

12. የኔዘርላንድ የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር (BZK) እና የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የስራ ግንኙነት ..... 37

አባሪ 1፡ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ታሪክ በቻርት ..... 39

ማጣቀሻዎች ..... 40

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ከግንቦት 26-30/2016 ዓ.ም የአባል ከተማ ከንቲባዎችን እና የትብብር መድረኩን የማኔጅመንት ዓባላት ያቀፈ ቡድን[1] ኔዘርላንድ አገር ትምህርታዊ ጉብኝት ማድረጉ ይታወቃል። ለተሻለ ተሞክሮነት የተመረጠችዋ ሀገር ኔዘርላንድ በተለይም የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG) እና የተመረጡ የኔዘርላንድ ከተሞች ያስመዘገቡት የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ተጨባጭ ውጤት ለተሻለ ተሞክሮነት የሚያበቃት ነው። ከኔዘርላንድ ከተሞች የተገኙ አዳዲስ እውቀቶች እና ልምዶች ለብቻቸው በሌላ ሰነዶች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ መሰል ተቋም ከሆነው ከኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ መስኮች የሚከተሉትን ያጠቃልላል። የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ታሪካዊ አመሰራረት፣ የኔዘርላንድ ያልተማከለ አስተዳደር፣ የማህበሩ አባላት እና የአባል ከተሞች ተሳትፎ፣ የማህበሩ ቁልፍ ተግባራት በዋናነት የከተሞች ድምጽ እና የአድቮኬሲ ስራዎች፤ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የአቅም ግንባታና የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶች፤ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲሁም አለም አቀፉ የኔዘርላንድ የከተሞች  ማህበር (VNGi) እንደ መልካም ተሞክሮ በመውሰድና በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ወደ ስራ ለመተርጎም ያስችል ዘንድ ተሞክሮ የተቀመሩባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው።

ቡድኑ የተሻለ ተሞክሮ ለማግኘት የሚመለከታቸው የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አመራሮችንና ባለሙያዎችን እንዲሁም የዘርፉ ልዩ ልዩ ተዋናዮች በገለጻዎች፤ በጉብኝቶች፤ መረጃዎችን በፎቶ ግራፍና ቪዲዮ አማካይነት በመቅረጽ፤ የተለያዩ ዶክመንቶችን በማሰባሰብ ልምዶችን የወሰደ ሲሆን ለሀገራችን

---

[1] የተሳታፊዎች ዝርዝር

1. አቶ አንዱዓለም ጤናው፤ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ዳይሬክተር ጀነራል- የልዑክ ቡድኑ መሪ፣
2. ክቡር አቶ ሀርቢ ቡሕ፤ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ- አባል፣
3. ክቡር አቶ እንዳለ ስጦታው፤ የወልቂጤ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ- አባል፣
4. ክቡር አቶ ኤልያስ ካሕሳይ፤ የመቐለ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ- አባል፣
5. አቶ ዘሪሁን ወርቅነህ፤ ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ- አባል፣
6. አቶ ዘገዬ ሀብትዬ ፤ ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ- አባል፣
7. አቶ ሀይለማርያም ጌጡ፤ ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ- አባል፣
8. ወ/ሮ ጣናወርቅ በላይነህ፤ ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ- አባል፣
9. አቶ ይበልጣል ይመኑ፤ ከኔዘርላንድ ማዘጋጃቤቶች ማህበር (VNGi)- አባል፣

ይጠቅማሉ ያላቸውን ተሞክሮዎች በዚህ ሰነድ ውስጥ በስፋት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ የዚህ ሰነድ አላማ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበርን በአደረጃጀት እና በአሰራር ዙሪያ ልምድ በመውሰድ ለአገራችን በሚስማማ መልኩ ቀምሮ ለመተግበር ነው፡፡

## 1. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG) ምስረታ ታሪክ

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ መሰል ተቋም የሆነው የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (Vereniging van Nederlandse Gemeenten, VNG) የተቋቋመው እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1912 በ28 ከተሞች ሲሆን የተቋቋመበትም ዓላማ የኔዘርላንድ ከተሞችን በመወከል ፍላጎታቸውን ለማስተጋባት ነበር፡፡ መጀመሪያ አካባቢ ከተሞች እርስ በእርስ እንዲተባበሩ፣ ልምዳቸውን እና እውቀታቸውን እንዲለዋወጡ መድረክ ሆኖ አገልግሏል፡፡ በመቀጠልም በሚዘጋጁ አገራዊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ላይ የአባላቱን ፍላጎት መሰረት በማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖዎችን በመፍጠር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ምስረታ እና በወቅቱ በኔዘርላንድ ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የከተሞች መስፋፋት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ታሪካዊ መስተጋብር እንደፈጠረ ይነገራል፡፡ ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ ማህበሩ አድማሱን በማስፋት ለአባላቶቹ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን በመስጠት ሚናውን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ (VNG, 2023)

በአሁን ወቅት የማህበሩ ተቀዳሚ ተግባሮች ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም አንደኛ ለአባላት ጥብቅና መቆም እና በአገር አቀፍ ደረጃ ጥቅሞቻቸውን ወክሎ መሟገት፡፡ ሁለተኛ ለከተሞች አገልግሎቶችን በመስጠት መደገፍ፡፡ ሦስተኛ በአባላት መካከል የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ መድረክ ሆኖ ማገልገል ናቸው፡፡



*ፎቶ 1፦- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ቢሮ ህንጻ በከፊል*

## የተገኙ ትምህርቶች

### ሀ/ ታሪካዊ መሰረት (Historical Foundations)

- ማህበሩ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1912 የተቋቋመው በከተሞች ከህዝብ ቁጥር መጨመር እና ከአገልግሎት ፍላጎት ጋር ተያይዞ የተከሰተውን ውስብስብነት በእውቀት ለመፍታት ዓላማን ያነገበ መሆኑ እና የኢትዮጵያ ከተሞችን በአሁን ወቅት ተመሳሳይ ፈተናዎች እያጋጠማቸው በመሆኑ ትብብር መድረኩን በማጠናከር የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል እንደሚገባ ትምህርት ተወስዷል።
- በኔዘርላንድ የከተሞች ማህበር እንዳደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክም የከተሞችን የጋራ ጥቅም የሚወክልና የሚከራከርበት መድረክ እንዲሆን ማጠናከር እንደሚገባ።
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር በፎቶ 1 እንደተመለከተው ለቢሮ እና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል የራሱ የሆነ ታሪካዊ ህንጻ ያለው መሆኑ።

### ለ/ ተቋማዊ እድገት (Organizational Development)

- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ልክ እንደ ኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ወሰኑን እና አገልግሎቱን ቀስ በቀስ የማስፋት እና የአባል ከተሞችን ፍላጎት ለማሟላት መስራት እንዳለበት ትምህርት ተወስዷል።
- ከትብብር መድረክነት ባሻገር ወደ ሀገራዊ ፖሊሲዎች እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ወደሚያደርግ ተቋም መሸጋገር ይኖርበታል።


### ሐ/ ተቋማዊ ቀጣይነት (Institutional Continuity)

- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ላለፉት አስርት አመታት ለኔዘርላንድ ከተሞች አገልግሎት ሲሰጥ እንደቆየው ሁሉ ትብብር መድረኩም ቀጣይነት ያለው አገልግሎት ለከተሞች ሊሰጥ ይገባል።

## 2. ስለ ኔዘርላንድ ከተሞች አጭር መረጃ

ኔዘርላንድ ልዩ ባህሪያት እና የአስተዳደር መዋቅር ያሏቸው የተለያዩ ከተማዎች አሏት። በኢኮኖሚ፣ በባህላዊ እና በፖለቲካዊ ተፅእኖዎቻቸው ታዋቂ የሆኑ እንደ አምስተርዳም፣ ሮተርዳም፣ ሄግ እና ዩትሬክት ያሉ ከተሞች ተጠቃሾች ናቸው። የኔዘርላንድ ከተሞች በከፍተኛ የኑሮ የጥራት ደረጃቸው፣ ውጤታማ የህዝብ ማመላለሻ ስርዓቶች እና ፈጠራ በተሞላበት የከተማ ፕላን ትግበራ ይታወቃሉ። ከተሞቻቸው ለአለም አቀፍ ንግድ፣ ፋይናንስ እና ቴክኖሎጂ ማዕከል በመሆን በማገልገል በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

በኔዘርላንድ 93.18 በመቶ የሚሆነው ህዝቧ በከተማ ውስጥ ይኖራሉ። ይህም በአውሮፓ ውስጥ ካሉት ከፍተኛ ከተሜ ከሚባሉት ሀገራት አንዷ ስትሆን የከተሞች መስፋፋት ለኔዘርላንድ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል። በሌላ በኩል ለቀጣይ ትውልድ የመኖሪያ አካባቢን ምቹ ማድረግ እና የአካባቢ ጤና ጉዳዮች ለከተሞች ተግዳሮቶች መሆናቸው አይቀሬ ነው። (Statista, 2023)




***ግራፍ 1፡- የኔዘርላንድ የከተሜነት እድገት በመቶኛ እ.ኤ.አ ከ2013 እስከ 2023***

## 3. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባልነት

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሁሉንም የኔዘርላንድ ከተሞችን የሚወክል ሲሆን ማህበሩ በኔዘርላንድ የሚገኙ 342 ከተሞችን በአባልነት አቅፎ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ከተሞቹ የማህበሩ አባል መሆናቸው ልዩ ልዩ ህግ ነክ ምክሮችን፣ ስልጠናዎችን እና የአባላትን ፍላጎት በአገር አቀፍ ደረጃ

ተሰሚነት እንዲኖረው ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ከተሞቹ በጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች የጋራ መፍትሄ እንዲያስቀምጡ እና በትብብር እንዲሰሩ እና የተሞክሮ ልምድ እንዲለዋወጡ መድረክ ፈጥሮላቸዋል። (VNG, 2023)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባል ለመሆን እንደመስፈርት ከተቀመጡ ጉዳዮች መካከል በኔዘርላንድ አገር በህጋዊ መንገድ የተዋቀረ ማንኛውም ከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት ይገኝበታል። ሌላው መስፈርት የማህበሩ አባል ለመሆን ለትብብር እና አብሮ ለመስራት ቁርጠኝነት መኖር ነው። የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባል መሆን የሚፈልጉ ከተሞች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች በእውቀት እና ልምድ መጋራት መድረኮች ለመሳተፍ፣ ለአባላት ፍላጎቶች በጋራ ጥብቅና ለመቆም እና በማህበሩ በሚዘጋጁ መድረኮች ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ማሳየት አለባቸው። የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባል ለመሆን በማህበሩ የተቀመጡ ልዩ ልዩ ህጎችን እና ደንቦችን ማክበር ሌላው በመስፈርትነት የተቀመጠ ነው። የማህበሩ አባል ለመሆን ሌላው መስፈርት በማህበሩ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ በተለይም በጠቅላላ ጉባኤዎች፣ በስራ አስፈጻሚ ቦርድ እና ኮሚቴዎች ውስጥ መሳተፍን ያካትታል። በጠቅላላ ጉባኤ በሚወሰነው ውሳኔ መሰረት አመታዊ የአባልነት መዋጮ በወቅቱ ለመክፈል ፍቃደኛ መሆን እንዳለባቸውም በመስፈርትነት ተቀምጧል። አመታዊ የአባልነት መዋጮዎች ማህበሩ ለአባላት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችን በገንዘብ ለመደገፍ ይረዳል።




*ካርታ 1፡- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባል ከተሞችን የሚያሳይ ካርታ*

## የተገኙ ትምህርቶች

- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉንም (342) ከተሞችን በአባልነት ያቀፈ እና እነዚህን ከተሞች በመወከል ፍላጎቶቻቸውን እና የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመንግስት በማቅረብ መፍትሄ የሚያሰጥ ተቋም መሆኑ፡፡
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባላት በሚዘጋጁ ጠቅላላ ጉባኤዎች ሳይንጠባጠቡ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆናቸው፡፡
- በኔዘርላንድ የሚገኙ ሁሉም ከተሞች በአስገዳጅነት የማህበሩ አባል መሆን አሰራር መኖሩ፡፡ ይህም ውክልናን እና ተሳትፎን የሚያበረታታ መሆኑ፡፡
- የማህበሩ አባላት አመታዊ የአባልነት ክፍያቸውን ሳያንጠባጥቡ መክፈላቸው ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ፡፡
- የማህበሩ የአባልነት መዋቅር የተለያዩ (ትናንሽ እና ትላልቅ ከተሞችን ጨምሮ) የከተሞች ፍላጎቶችን ለመወከል በሚያስችል መልኩ መደራጀቱ፡፡

- የማህበሩ የአባልነት ሞዴል ንቁ ተሳትፎን እና ቀጣይነት ያለው ግብረመልስ ከአባላቱ በማበረታታት ይታወቃል። ይህም የማህበሩ የትኩረት መስኮች ከከተሞች ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
- የማህበሩ የአባልነት መዋቅር እና የተሳትፎ ስልቶች ከተሞች እንዴት በብቃት መደራጀት እና በእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ መድረኮች እና የስልጠና መድረኮች አቅሞቻቸውን መገንባት እንደሚችሉ ምሳሌ ሆኖ ማገልገሉ።

## 4. ያልተማከለ አስተዳደር በኔዘርላንድ (Tradition of local democracy and decentralization)

ኔዘርላንድ ያልተማከለ አስተዳደርን በምትከተለው የመንግስታዊ አወቃቀር ስልት ውስጥ በማካተት እና ተግባራዊ በማድረግ የረጅም ጊዜ ልምድ ያላት አገር ናት። የሀገሪቱ መንግስታዊ አወቃቀር ማእከላዊ መንግስትን፣ 12 የክልል መንግስታትን፣ ከተሞችን እና የአውሮፓ ህብረትን ባካተተ መልኩ በአራት እርከኖች ተዋቅሯል። ይህ አወቃቀር ከተሞችን በዋናነት በስፓሺያል ፕላኒንግ፣ በህብረተሰብ ጤና እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ራሳቸውን በመቻል ውሳኔ እንዲሰጡ አስችሏቸዋል። እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1980ዎቹ እና በ1990ዎቹ የከተሞችን እና የክልሎችን የአገልግሎት ቅልጥፍና እና ምላሽ ሰጪነት ለማሳደግ ያለመ የለውጥ ሪፎርሞችን ተግባራዊ በማድረግ ያልተማከለ አስተዳደር በከፍተኛ ሁኔታ ሊጠናከር እና ስር ሊሰድ ችሏል። (Ministry of the Interior and Kingdom Relations, 2022)

በኔዘርላንድ ከተሞች የፅዳትና ውበት፣ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አስተዳደር እና የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት የሚሰጡ መሰረታዊ የመንግስት መዋቅሮች ናቸው። እያንዳንዱ ከተማ የሚተዳደረው በከተማ ከንቲባ፣ በከተማ ምክር ቤት እና በአልደርማን (ምክትል ከንቲባ) ነው፤ ስልጣናቸውም የከተማ ልማት ፖሊሲዎችን ማስፈጸም እና የህግ አውጪውን መቆጣጠርን ያካትታል። (Netherland | The Global State of Democracy, n.d.)




*ካርታ 2፦ የኔዘርላንድ አገር ካርታ*

የኔዘርላንድ ሕገ- መንግሥት በተለይም አንቀጽ 124 እና 132 ያልተማከለ አስተዳደር መርሆዎችን በዝርዝር ያስቀምጣል፤ ክልሎችን እና ከተሞችን የውስጥ ጉዳዮቻቸውን የመቆጣጠር ሥልጣን ይሰጣል። (VLEX, 2018) ይህ ህጋዊ መሰረት ከተሞች እና የአካባቢ አስተዳደሮችን ይደግፋል፣ ከተሞች የነዋሪዎቻቸውን ልዩ ፍላጎቶች በማንፀባረቅ ፖሊሲዎችን እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ በማጣጣም እንዲቀርፁ ያስችላቸዋል። (CoR, nd) እ.ኤ.አ ከ2015 ጀምሮ በማህበራዊ ፖሊሲ ዘርፎች በዋናነት የወጣቶች እንክብካቤ፣ የረጅም ጊዜ እንክብካቤ እና የገቢ ድጋፍ የመሳሰሉ የስራ ድርሻዎች ከማእከላዊ መንግስት ወደ ከተሞች ተሸጋግረዋል። (Tandfonline, 2018) ይህ ያልተማከለ አስተዳደር ከተሞች ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ያለመ ነው። በኔዘርላንድ የአካባቢ ዲሞክራሲ እና ያልተማከለ አስተዳደር የፖለቲካ እና ህገ-መንግስታዊ ማዕቀፉ መሠረታዊ ገጽታ ነው። (VNG International, 2017)

## 5. የጥብቅና እና የአባል ከተሞች ድምጽ (Advocacy and Voice)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የከተሞችን ፍላጎት በማእከላዊ መንግስት እና በፓርላማ ደረጃ ከተሞችን በመወከል ድምጽ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ተቋማት ጋር ከተሞችን በመወከል ውይይቶችን በማድረግ ጥቅሞቻቸው እንዲከበር ይታገላል። ከተሞች ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ፖሊሲዎች ላይ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ከማእከላዊ መንግስት፣ ከአውሮፓ ህብረት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀራረብ በንቃት ይሳተፋል። ማህበሩ ለማእከላዊ መንግስቱ ምክር ይሰጣል።

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የአድቮኬሲ ጥረቶች በዋናነት የከተሞች የፋይናንስ ድጋፍ፣ ማህበራዊ ዋስትና እና የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው። የማግባባት ስራን በተመለከተ ማህበሩ በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት የአባል ከተሞች ጥቅምን ለማስጠበቅ የከተሞች ድምጽ በአግባቡ መደመጡን

ያረጋግጣል። የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ለከተሞች እንደ አንድ ድምፅ ሆኖ ከተሞችን በመወከል በተለያዩ መድረኮች ፍላጎታቸው እና ስጋቶቻቸውን ይገልጻል። (VNG, 2023)

## የተገኙ ትምህርቶች

- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ተቀዳሚ ሚና አባል ከተሞችን በመወከል ለማእከላዊ መንግስት በስትራቴጂክ ጉዳዮች ዙሪያ ምክረ ሃሳብ እና ገንቢ ግብአት በማቅረብ የከተሞች ልማትን እና አገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን መሆኑ።
- ማህበሩ በብሔራዊ የከተማ ልማት ፖሊሲ ዝግጅት እና ክለሳ ሂደት ውስጥ ከተሞችን በመወከል ፍላጎታቸውን እና ያጋጠማቸውን ችግሮች በሰነዶች ውስጥ እንዲካተቱ ጠንካራ እና የተዋሃደ ድምጽ (strong and unified voice) ሆኖ ማገልገሉ።
- የማህበሩ የጥብቅና ጥረቶች የአገልግሎት አቅርቦትን፣ የበጀት ድልድልን እና የአዳዲስ ህጎችን እና ደንቦችን ትግበራን ጨምሮ ሰፊ የፖሊሲ ዘርፎችን መሸፈኑ ለትብብር መድረኩ እንደትምህርት ተወስዷል።
- የማህበሩ ተሟጋችነት (advocacy) የአባላቱን ተግዳሮቶች እና ፍላጎቶች በጥልቀት በመረዳት ላይ የተመሰረተ መሆኑ፣ እና ይህም በሚገባ በመረጃ የተደገፈ እና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ መዋሉ።
- የማህበሩ ተሟጋችነት ሰፊ የአባልነት መሰረት ያለው መሆኑ እና በአባላቶቹ ንቁ ተሳትፎ የተደገፈ መሆኑ።
- የማህበሩ ተሟጋችነት ሚና ከሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘልቅ ሲሆን በአውሮፓ ህብረት እና በሌሎች አለም አቀፍ መድረኮች የኔዘርላንድ ከተሞችን መወከል መቻሉ።
- የማህበሩ ተሟጋች ጥረቶች የሚደገፉት ለአባል ከተሞች ቴክኒካል እና ስልታዊ ድጋፍ በሚሰጡ የባለሙያዎች ቡድን እና የፖሊሲ ባለሙያዎች መሆኑ።

## 6. አገልግሎት አሰጣጥ

ማህበሩ ለአባላቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። የህግ ድጋፍ፣ የምክር አገልግሎት እና ከተሞችን ለማዘመን የሚረዱ የስልጠና ፕሮግራሞችን ያመቻቻል፤ ከተሞች ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሄዎችን በማመላከት እና እንዲተገበሩ በማድረግ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ የጥራት መጓደሎች እንዲቀረፉ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪም የእውቀት እና ልምድ ልውውጥ አውደጥናቶችን በማዘጋጀት፣ በተለያዩ ዘርፎች ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፣ የከተማ ፕላን እና የህዝብ አገልግሎት

አሰጣጥን የመሳሰሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሞዴል ማንዋሎችን፣ ቱልኪቶችን እና ዝርዝር ማዕቀፎችን በማዘጋጀት፣ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት፣ የጥብቅና አገልግሎት፣ የአለም አቀፍ ትብብር አገልግሎቶችን ይሰጣል። (VNG, 2023)

ማህበሩ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ለከተሞች የጥሪ ማእከል (call center)፣ የመረጃ አቅርቦት (deliver data) እና ስለ አዳዲስ ህጎች እና መመሪያዎች መረጃ መስጠት፣ ለከተሞች የግዢ አገልግሎት (purchase common goods)፣ ICT አገልግሎትን ጨምሮ ሰፊ አገልግሎቶችን በመስጠት ተጠቃሾች ናቸው። የማህበሩ 20 በመቶ የሚሆኑ ሰራተኞች የማግባባት (Lobby) ስራዎችን የሚሰሩ ሲሆን 80 በመቶ የሚሆኑ ሰራተኞች አገልግሎት በመስጠት የተሰማሩ ናቸው።




***ፎቶ 2፦ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የህትመት ውጤቶች በከፊል***

## የተገኙ ትምህርቶች

- ማህበሩ ለአባላት ከተሞች የጥሪ ማእከል፣ የመረጃ አቅርቦት እና ስለ አዳዲስ ህጎች እና መመሪያዎች መረጃን ጨምሮ ሰፊ አገልግሎቶችን መስጠቱ።
- ማህበሩ የሳይበር ወንጀል ቡድንን (cybercrime team) ጨምሮ የአባል ከተሞችን እያደገ ከመጣው ዲጂታል ተግዳሮቶች ለማገዝ ልዩ የአይሲቲ አገልግሎቶችን (ICT services) መስጠት መቻሉ።
- የማህበሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል የአባል ከተሞችን የተለያዩ ፍላጎቶችን እና አቅሞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተነደፈ ሲሆን ለተለያዩ መጠን ላላቸው ከተሞች የተዘጋጀ መፍትሄዎችን ማካተቱ።

- የማህበሩ አገልግሎት አሰጣጥ ከተሞች የሚያጋጥሟቸውን የአሠራር እና የአስተዳደር ተግዳሮቶች በጥልቀት በመረዳት የተደገፈ መሆኑ።
- የማህበሩ አገልግሎት አሰጣጥ ከተለዋዋጭ የከተሞች ፍላጎቶች፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና ደንቦች ጋር ለመራመድ በየጊዜው እየተሻሻለ መሆኑ።
- የማህበሩ አገልግሎት አሰጣጥ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረገው "በአመታዊ የአባልነት ክፍያዎች" (membership fees) እና "በአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ መዋጮ" (Collective Implementation Mechanism)[2] አማካኝነት ሲሆን ይህም የአቅርቦቶቹን ዘላቂነት ማረጋገጥ መቻሉ።
- የማህበሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል በጋራ የመማማር እና የእውቀት ልውውጥን አስፈላጊነት ማጉላት መቻሉ፣ አባላት ለማህበሩ አገልግሎቶች መሻሻል ንቁ አስተዋፅዖ ማድረጋቸው።

## 7. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የልምድ ልውውጥ መድረኮች (VNG-Platform)

ማህበሩ ለከተሞች የአቅም ግንባታ ስልጠና እና በአባል ከተሞች መካከል የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ አውደጥናቶችን እና ኮንፈረንሶችን በየጊዜው ያዘጋጃል። እነዚህ መድረኮች ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች እርስ በእርስ ለመማማር እና ለሚያጋጥሟቸው የጋራ ተግዳሮቶች የጋራ መፍትሄ የሚያስቀምጡበት መድረኮች ናቸው። ማህበሩ በአባላቱ መካከል የአቅም ግንባታ፣ የእውቀት እና የልምድ ልውውጥን ለማሳለጥ በርካታ አማራጮችን ይጠቀማል። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታል:-

### ሀ/ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አካዳሚ (VNG Academy- Hague Academy for Local Governance)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አካል የሆነው ለትርፍ ያልተቋቋመው የሄግ አካዳሚ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን በተግባር ላይ ያተኮሩ ከከተሞች ተጨባጭ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙ የተለያዩ የስልጠና ፕሮግራሞችን ቀርጾ ተግባራዊ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። የስልጠና ፕሮግራሞቹም አጫጭር የስልጠና መርሃ ግብሮችን፣ የማስተርስ ዲግሪ ትምህርቶችን እና የጥናት ጉብኝቶችን (study visits) ያካትታል። የስልጠና ፕሮግራሞችም መልካም አስተዳደር፣ ሰላም ግንባታ፣ አካታች የከተማ ፕላን እና አስተዳደር፣ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፣ አካታች የአገልግሎት አቅርቦት እና ዘላቂ የልማት ግቦች፣

[2] "አስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ መዋጮ " ማለት 3€ በአንድ ነዋሪ ተሰልቶ በከተማው ጠቅላላ የህዝብ ብዛት ተባዝቶ አባል ከተሞች ለተጨማሪ ልዩ ስልጠናዎች እና አውደጥናቶች በፍላጎት (optional) ለማህበሩ የሚከፍሉት ክፍያ ነው።

ስማርት ሲቲ፣ ያልተማከለ አስተዳደር እና ሌሎችንም ያካትታል፡፡ አካዳሚው ከ190 በላይ የጥናት ጉብኝቶችን (study visits) ወደ ኔዘርላንድ እና ከኔዘርላንድ ውጪ ለተለያዩ ድርጅቶች አዘጋጅቷል፡፡ በአካዳሚው የጥናት ጉብኝት የተመቻቸላቸው ተቋማት በፎቶ 4 ተዘርዝረዋል፡፡

**The Academy has convened over 190 study visits to organisations in the Netherlands and abroad. These study visits include:**

- **Amsterdam Integrity Bureau**
- **Amsterdam Economic Board**
- **Court of Audit of The Netherlands**
- **Dutch Water Authorities and the** *Room for the River* **project**
- **European Commission**
- **EVA Lanxmeer Ecological Neighbourhood in Culemborg**
- **Father Centre The Hague** *(gender equality project)*
- **Genesis Farm, Municipality of Bishoftu (Ethiopia)**
- **Greenport Aalsmeer World Centre for Horticulture**
- **International Criminal Court**
- **IRADO Waste Management Facility**
- **Local economic development projects (Jordan, Palestine)**
- **Local Communities Support and Loan Fund (Tunis)**
- **Maeslantkering Storm Surge Barrier**
- **Ministries of Interior and Labour (Morocco, Jordan, Tunisia)**
- **Municipal Ombudsman of The Hague**
- **Netherlands' House for Democracy and the Rule of Law**
- **Public Prosecutor's Office**
- **Radio Netherlands Training Institute**
- **Regional Police Haaglanden**
- **World of Westland, International knowledge centre in glasshouse horticulture**
- **Yes!Delft, business and tech incubator**

***ፎቶ 3፡- የጥናት ጉብኝት የተመቻቸላቸው ተቋማት በከፊል***

***ፎቶ 4፡- የሄግ አካዳሚ ሎጎ***

የአካዳሚው ተልእኮ ወቅታዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ ከተለያዩ አገራት ከተሞች ለተውጣጡ የከተማ አመራሮች እና ባለሙያዎች በስልጠና እውቀታቸውን እና ክህሎታቸውን መገንባት ነው፡፡ በፎቶ 5 እንደተመለከተው በሄግ አካዳሚ የሥልጠና መርሃ ግብሮችን ያጠናቀቁ ተሳታፊዎች ፕሮፌሽናል ሰርተፍኬት ያገኛሉ፡፡




***ፎቶ 5፡- የሄግ አካዳሚ ስልጠና ለሚያጠናቅቁ ተሳታፊዎች የሚሰጥ ሰርቲፊኬት ናሙና***

አካዳሚው በተለያዩ አገራት የሚገኙ ከተሞች ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እንዲጎለብት በትኩረት እየሰራ ይገኛል። አካዳሚው ከተሞች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እና አሰራራቸውን በማዘመን የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል እና የዜጎችን ተሳትፎ ለማሳደግ እገዛ ያደርጋል። (The Hague Academy for Local Governance, n.d.) በዚህ ዙሪያ ስልጠና መስጠት ስማርት ሲቲን ተግባራዊ ለማድረግ እና የዲጂታላይዜሽን ማነቆዎችን ለመፍታት ይረዳል። እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 2017 እስከ ጥቅምት 2019 የቀድሞ የሄግ ከንቲባ የነበሩት የተከበሩ ፓውሊን ክሪኬ በአንድ ወቅት የሚከተሉትን ብለው ነበር፡-

> *"ባለፉት አስር አመታት የሄግ አካዳሚ ለሄግ ከተማ ተልዕኮ፣ ሰላምን፣ ፍትህን እና መረጋጋትን በአለም ላይ በማስፈን ተጨባጭ እና ተግባራዊ በሆነ መንገድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል"*




***ፎቶ 6፡- የሄግ ከተማ ክቡር ከንቲባ ስለ አካዳሚው የተናገሩት***

አካዳሚው ከአለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG International) ጋር በመተባበር በአለም አቀፍ ትብብር ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ አላማውም በኔዘርላንድም ሆነ በውጭ የሚገኙ ከተሞችን አቅም በማጠናከር መልካም አስተዳደር እና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ማስቻል ነው፡፡ (International Cooperation Agency of the Association of Netherlands Municipalities, n.d.) ይህ አለም አቀፋዊ ትኩረት አካዳሚው በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ከተሞች መካከል የእውቀት ልውውጥ እና ትብብርን በማጎልበት በአለም አቀፍ ደረጃ ለአቅም ግንባታ ስራዎች አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ያስችለዋል፡፡ ስለ አካዳሚው የበለጠ ለማንበብ የሚከተለውን ድረገጽ ይክፈቱ፡- https://thehagueacademy.com/

በሄግ አካዳሚ ስልጠና ለመከታተል የክፍያ መጠኑ እንደየኮርስ ዓይነቱ ይለያያል፡፡ ለኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባላት ተሳታፊዎች ለአጫጭር ስልጠና ኮርሶች የምዝገባ ክፍያ በአጠቃላይ € 3,595 በአንድ ሰው ይከፈላል፡፡ ይህ ክፍያ በስልጠና ፕሮግራሙ ወቅት ለስልጠና ቁሳቁስ፣ ለምሳ እና ለረፍረሽመንት ጨምሮ ሁሉንም ከስልጠና ጋር የተያያዙ ወጪዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን የትራንስፖርት ወጪን ግን

አያካትትም። ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የአንድ ድርጅት ባልደረቦች በአንድ ኮርስ ላይ ከተሳተፉ ቅናሽ ይደረጋል። እንደዚህ አይነት ቅናሾች አባላት ለብዙ አመራሮችና ባለሙያዎች የመማር እድሎችን እንዲሰጡ አስችሏቸዋል። የሄግ አካዳሚ በርካታ የስኮላርሺፕ ፕሮግራሞችን ያመቻቸ ሲሆን ይህም በስልጠና ኮርሶች ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ባለሙያዎችን እና አመራሮችን ለመደገፍ ነው። እነዚህ ስኮላርሺፖች ከተለያዩ የአለም ክፍሎች የተውጣጡ ግለሰቦችን ችሎታ እና እውቀት ለማሳደግ የተነደፉ ናቸው። የኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለመካከለኛ ደረጃ ፕሮፌሽናሎች የስኮላርሺፕ ፈንድ በየአመቱ የሚመድብ ሲሆን ለስልጠና ስኮላርሺፕ አመልክተው ያለፉ ሰዎች ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖላቸው በአካዳው እንዲከታተሉ ይደረጋል። (The Hague Academy for Local Governance, n.d.)



*ፎቶ 7፡- የሄግ አካዳሚ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና አካታች አስተዳደር ኮርስ ሰልጣኞች በከፊል*

አካዳሚውን በፋይናንስ የሚያግዙ ተቋማት የኔዘርላንድ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ጂአይዚ፣ አለም ባንክ፣ ዩኤንዲፒ፣ የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን እና ዩኤን ሀቢታት ናቸው። እ.ኤ.አ. እስከ 2018 በተሰበሰበ መረጃ የስልጠናው ተሳታፊዎች ብዛት በመቶኛ በምናይበት ጊዜ 33 በመቶው ከማእከላዊ መንግስታት፣ 23 በመቶው ከክልል እና ከተማ መዋቅር፣ 5 በመቶው ከጥናትና ስልጠና ተቋማት፣ 27 በመቶው መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ 12 በመቶው ዶነሮችና የልማት ድርጅቶች ናቸው።

አካዳሚው ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር አለው። ከ25 በላይ ሰራተኞችን ከተለያዩ አገራት በመቅጠር እና ወደ 200 የሚጠጉ አለምአቀፍ ባለሙያዎችን በአሰልጣኝነት በፑል (trainers pool) በማሰባሰብ ስራውን ያከናውናል። ይህ የተለያየ የቡድን ስብጥር ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የሥልጠና መርሃ ግብሮችን ለማቅረብ እና የሚሰጡ ስልጠናዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመጡ ተሳታፊዎችን ፍላጎት እንዲያሟሉ ለማድረግ አስፈላጊ ነው። የአሰልጣኞች ፑል አባላት ስልጠና ከሚሰጡባቸው ርዕሰ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

> *"Fiscal Decentralization & Local Finance; Local Economic Development; Development, Gender & Participation; Post- Conflict and Social and Economic Development; Local Governance and Rural Development; Gender Responsive Governance; Local Development Finance; Inclusive Local Service Delivery & SDG, Water Governance; Integrity and Anti-Corruption; Disaster Management & Climate Resilience, Human Rights & the Rule of Law, Smart & Resilient Cities, Leadership & Municipal Management, Citizen Participation & Inclusive Governance, Social Affairs & Employment, Lobby & Advocacy, Migration & Cities"*

አካዳሚው በዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን ከዛ በመቀጠል ከፍተኛው የስልጣን እርከን ከፍተኛ የፕሮግራም ማናጀር እና አሰልጣኝ ነው። ይህ የአመራር መዋቅር የአካዳሚውን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ ለመምራት እና ስራዎቹን በብቃት ለማስተዳደር ወሳኝ ነው። አካዳሚው በየአመቱ ከ1000 በላይ ግለሰቦችን ከ90 በላይ ሀገራት በማሰልጠን የአካባቢያዊ አስተዳደር ጉዳዮችን በአለም አቀፍ ደረጃ የማሳደግ ተልእኮውን ያሟላል።

## ለ/ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሰልጣኞች ፕሮግራም (VNG Trainee programme)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሰልጣኝ ፕሮግራም የተዘጋጀው በአካባቢ አስተዳደር እና በህዝብ አስተዳደር (local governance and public administration) ውስጥ ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ወጣት ተመራቂዎች ነው። ፕሮግራሙ ሰልጣኞች በኔዘርላንድ ከሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች ጋር በቀጥታ እንዲገናኙ ያስችላቸዋል፣ ይህም በተግባራዊ ልምድ እና በማዘጋጃ ቤት ስራዎች እና ፖሊሲ አወጣጥ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ፕሮግራሙ በከተማ ስራ አመራር አዲስ የሰለጠነ ባለሙያዎችን ለማፍራት አስፈላጊ ነው። ፕሮግራሙ ያልተማከለ አስተዳደር፣ የከተማ ስራአመራር እና የዜጎች ተሳትፎን ጨምሮ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። ሥርዓተ ትምህርቱ የተዋቀረው የንድፈ

ሃሳባዊ ግንዛቤዎችን ከተግባራዊ አተገባበር ጋር በማጣመር ሰልጣኞች የተማሩትን በገሃዱ ዓለም ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ በማረጋገጥ ነው። (VNG, 2023)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሰልጣኞች ፕሮግራም ከአንድ እስከ ሁለት አመት የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ጊዜ ሰልጣኞች በተለያዩ ማዘጋጃ ቤቶች ይመደባሉ። ይህም የተለያዩ የአካባቢ ሁኔታዎችን እና ተግዳሮቶችን እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል። (International Cooperation Agency of the Association of Netherlands Municipalities, 2023) በፕሮግራሙ በሙሉ ተሳታፊዎች በማዘጋጃ ቤት አስተዳደር ላይ ክህሎቶቻቸውን እና እውቀታቸውን ለማዳበር ያለመ አውደ ጥናቶች፣ ሴሚናሮች እና የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል። (VNG, 2023)

ለሰልጣኝ ፕሮግራም ብቁ ለመሆን እጩዎች በአጠቃላይ ከከተማ ስራአመራር፣ ከህዝብ አስተዳደር፣ ከፖለቲካል ሳይንስ ወይም ተዛማጅ መስክ ጋር ተዛማጅነት ያለው የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ሊኖራቸው ይገባል። በተጨማሪም ለፕሮግራሙ ስኬት ጠንካራ የተግባቦት ችሎታ እና የከተማ አስተዳደር ፍላጎት አስፈላጊ ናቸው። (About the VNG, 2023) እጩዎች ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ለመሳተፍ እና ለአካባቢው ማህበረሰቦች አዎንታዊ አስተዋፅዖ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ማሳየት አለባቸው። ፕሮግራሙን ያጠናቀቁ እና የተመረቁ ተሳታፊዎች በከተማ አስተዳደር ውስጥ የስራ እድል የማግኘት እድላቸው ከፍተኛ ነው። (VNG International, 2023)



***ፎቶ 8፡- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የሰልጣኞች ፕሮግራም ተሳታፊዎች በከፊል***

## ሐ/ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ስቱዲዮ (VNG Studio (Webinars))

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ስቱዲዮ ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች በበይነመረብ በቀጥታ የመማር እድሎችን (online learning opportunities) በዌብናሮች እያቀረበ ይገኛል። ይህ ፕሮግራም በከተሞች መካከል የእውቀትና ልምድ ልውውጥን ለማመቻቸት እና ለተሳታፊዎች ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ያላቸውን አቅም ባሉበት ሆነው አቅማቸውን ለማሳደግ ያለመ ነው። ዲጂታል መድረኮችን በመጠቀም የማህበሩ ስቱዲዮ የከተሞች የእርስ በርስ መማርን ያበረታታል። (VNG, 2017)

የማህበሩ ስቱዲዮ ዌብናሮች በተለምዶ ዲጂታላይዜሽን፣ ስማርት ከተሞች፣ የማዘጋጃ ቤት ፋይናንስ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ስትራቴጂዎችን ጨምሮ በተለያዩ ጭብጦች ላይ ያተኩራሉ። እነዚህ ርዕሶች የሚመረጡት ከተሞች እያጋጠሟቸው ባሉ ወቅታዊ የህብረተሰብ ችግሮች ላይ በመመስረት ይዘቱ ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ጠቃሚ መሆኑን በማረጋገጥ ነው። (VNG International, 2023)

ዌብናሮች በባህሪያቸው መስተጋብራዊ እንዲሆኑ ተደርገው የሚዘጋጁ ሲሆን ውይይቶችን፣ የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜዎችን እና ተሳታፊዎች ልምዶቻቸውን እንዲያካፍሉ እድሎችን ይሰጣሉ። ያለፉት ዌብናሮች ቅጂዎች በተለያየ ምክንያት በቀጥታ መሳተፍ ለማይችሉ ሰዎች በመልቀቅ በሚመቻቸው ወቅት የውይይቶቹን ጭብጦች እንዲመለከቱ ይደረጋል። (VNG International, 2023)

በማህበሩ ስቱዲዮ ዌብናሮች ውስጥ መሳተፍ ሙያዊ እድገትን፣ የኔትወርኪንግ እድሎችን እና ከዘርፉ ባለሙያዎች ብዙ እውቀት ማግኘትን ጨምሮ በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣል። በተጨማሪም እነዚህ መርሃግብሮች ከተሞች በከተማ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ስላለው የቅርብ ጊዜ ተሞክሮዎች እንዲለዋወጡ በማድረግ ማህበረሰባቸውን በብቃት የማገልገል አቅማቸውን ያሳድጋል። (VNG, 2017)

ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ለቀጣይ ዌብናር በኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ወይም ለከተሞች በሚተላለፉ ማስታወቂያዎች መሰረት ይመዘገባሉ። የምዝገባ ሂደቱ ቀጥተኛ ሲሆን ተሳታፊዎች ከፍላጎታቸው ጋር ለሚጣጣሙ መርሃግብሮች በቀላሉ እንዲመዘገቡ ያስችላቸዋል። በአጠቃላይ የማህበሩ ስቱዲዮ ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች በልማትና በአገልግሎት መስክ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ እየሰራ ይገኛል። (VNG International, 2023)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ስቱዲዮ ዌብናር እና የቀጥታ ኩነቶችን ጨምሮ የተለያዩ የኦንላይን መድረኮችን ለማካሄድ የኦዲዮቪዥዋል ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በተሟላ ሁኔታ አሉት። እነሱም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- **የቪዲዮ ካሜራዎች፡-** ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ካሜራዎች ምስላዊ ይዘትን እና ሰነድ አቅራቢዎችን ለመቅረጽ ያገለግላል። (VNG International, n.d.)
- **ማይክሮፎኖች እና የድምጽ መቅረጽ መሳሪያዎች፡-** በኩነቶች ወቅት ጥርት ያለ ድምጽ ለመቅረጽ እና ውጤታማ ተግባቦት ለማከናወን ማይክሮፎኖች ጥቅም ላይ ይውላሉ። (VNG International, n.d.)
- **የመብራት መሳሪያዎች (Lighting Equipment)፡-** አቅራቢዎች ላይ በቂ ብርሃን በማብራት የቪዲዮ ጥራትን ለማሻሻል የመብራት ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ ይውላሉ። (VNG, n.d.)
- **ሶፍትዌር/ፕላትፎርሞች (Streaming Software/Platforms)፡-** የቀጥታ ስርጭት፣ ቀረጻ እና የዌብናርስ መስተጋብራዊ ክፍሎችን (interactive components of webinars) የሚያመቻቹ ሶፍትዌሮች ተሟልተዋል። (Association of Netherlands Municipalities, 2023)
- **የስልጠና መስጫ ወይም ልምድ ለመለዋወጥ የሚያለግሉ መሳሪያዎች፡-** እንደ ስክሪኖች ወይም ፕሮጀክተሮች ያሉ ለእይታ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ እና ስላይድ ለማሳየት ጥቅም ላይ ይውላሉ። (VNG International, nd)

የማህበሩ ስቱዲዮ በዌብናር ወቅት የኦዲዮ ቪዥዋል መሳሪያዎችን የሚያዘጋጅ፣ የሚቆጣጥር እና ብልሽት ሲያጋጥም የሚያስተካክል ቴክኒካል ባለሙያዎች ተሟልተውለታል። ሌላው ውይይቶችን የሚመሩ፣ ተሳታፊዎችን በጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜዎች የሚያሳትፉ እና ዝግጅቱ ያለችግር መሄዱን የሚያረጋግጡ አስተባባሪዎች ወይም አወያዮች ሚናቸውን እየተወጡ ይገኛል። ሰነዶችን፣ ፕረዘንቴሽኖችን የሚያዘጋጁ እና ሁሉም ይዘቶች ከዌብናሩ ዓላማ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ የቡድን አባላትም (Content Creators) አሉ። (VNG International, n.d.)

## መ/ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር መጽሔት (VNG Magazine)

መጽሔቱ በኔዘርላንድ ከተሞች መካከል የመረጃ ልውውጥን፣ የእውቀትና ልምድ ልውውጥን እና ትብብርን ለማመቻቸት የሚዘጋጅ ኦፊሴላዊ ሰነድ ነው። ዋና አላማው ለከተማ አመራሮችና

ባለሙያዎች አዳዲስ እውቀቶችንና ተሞክሮዎችን፣ የህግ ማዕቀፍ ለውጦችን እና አሰራሮችን ግንዛቤ መፍጠር ነው። (VNG, n.d.) መፅሔቱ የውይይት እና የመረጃ ልውውጥ መድረክ በመሆን ከተሞች ነዋሪዎቻቸውን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል የሚያደርጉትን ጥረት ይደግፋል። (Association of Netherlands Municipalities, 2024)

መደበኛ መጽሔቱ የማዘጋጃ ቤት ፋይናንስን፣ የከተማ ፕላንን፣ ዘላቂነትን፣ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እና የህዝብ ደህንነትን ጨምሮ ከከተማ አስተዳደር ጋር የተያያዙ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን ይሸፍናል። (VNG International, 2022) እያንዳንዱ እትም መጣጥፎችን፣ ጥናቶችን፣ ቃለ-መጠይቆችን እና የባለሙያዎችን አስተያየቶችን በማካተት ያቀርባል። ይህም ከተሞች የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች እና እድሎች ለመረዳት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። (VNG Magazine, 2024) መፅሄቱ በኔዘርላንድ ላሉ የከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ጭምር ይሰራጫል። (VNG International, 2022) መጽሄቱን ለበርካታ አንባቢያን ተደራሽ ለማድረግ በሁለቱም በዲጂታል እና በህትመት በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ ይሰራጫል። የዲጂታል እትም ብዙ ጊዜ የአንባቢያንን ተሳትፎ ለማሳደግ ተጨማሪ የመልቲሚዲያ ይዘቶችን ያካትታል። (Association of Netherlands Municipalities, 2024) መጽሔቱ ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ለአቅም ግንባታ አስፈላጊ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። በመጽሔቱ ላይ የሚቀርቡትን ምርጥ ተሞክሮዎች እና አዳዲስ እውቀቶችን ተግባራዊ በማድረግ ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን አሻሽለዋል። (VNG International, 2022)

### ሠ/ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ኩነቶች (VNG Events)

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የሚያዘጋጃቸው መድረኮች በከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት መካከል ለትብብር እና ትስስር (collaboration and networking) ትልቅ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። እነዚህ ኩነቶች የተቀረጹት ከተሞች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በእውቀት ለመፍታት እና ውጤታማ ስትራቴጂዎች እና ፖሊሲዎች ላይ ልምድ ለመለዋወጥ ነው። በአውደ ጥናቶች፣ በፕረዘንቴሽኖች እና ውይይቶች ተሳታፊዎች ለሚያጋጥሟቸው የጋራ ተግዳሮቶች ልምድ እንዲለዋወጡ አስችሏቸዋል። ማህበሩ ዓመታዊ ስብሰባዎችን፣ ኮንፈረንሶችን፣ ዌብናሮችን እና የአውታረ መረብ የቀጥታ ስብሰባዎችን እና አውደጥናቶችን ጨምሮ በርካታ የኩነት አይነቶችን ያዘጋጃል ። (VNG International, 2022)




*ፎቶ 9፡- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ካዘጋጃቸው የልምድ ልውውጥ መድረክ መካከል በከፊል*

## የተገኙ ትምህርቶች

- ማህበሩ ለአባል ከተሞች እውቀቶችን እና ልምዶችን እንዲያካፍሉ የተለያዩ መድረኮችን እና ፕሮግራሞችን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረጉና የአባል ከተሞች አመራሮችና ባለሙያዎች አቅማቸው በየጊዜው መገንባቱ፤ ለዚህ ማህበሩ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አካዳሚ፣ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሰልጣኞች ፕሮግራም፣ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ስቱዲዮ (VNG Studio (Webinars))፣ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር መጽሔት እንዲሁም የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ኩነቶች አባል ከተሞች ስልጠና እና ልምድ እንዲለዋወጡባቸው ማቋቋሙ።
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አካዳሚ (VNG Academy) ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በተለይም በፖሊሲ ዝግጅት፣ በፋይናንስ አስተዳደር እና በአገልግሎት አሰጣጥ መስጠቱ።
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሰልጣኝ ፕሮግራም (VNG Trainee programme) አዳዲስ ባለተሰጥኦ ወጣት ባለሙያዎችን ወይም በቅርብ ከዩንቨርሲቲ የተመረቁ ወጣቶችን በልዩ ልዩ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ልምድ እንዲያገኙ ፕሮግራም መቀረጹ እና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ።

- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ስቱዲዮ (VNG Studio) የኦንላይን ዌብናሮችን እና ወርክሾፖችን ማዘጋጀቱ እና ተግባራዊ ማድረጉ፤ ይህም የከተማ ከንቲባዎች፣ ሥራ አሥኪያጆች እና የህዝብ ተመራጮች አዳዲስ መረጃዎችን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ከራሳቸው ቢሮ ሆነው እንዲያገኙ ማስቻሉ።
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር መጽሄት (VNG Magazine) እንደ መደበኛ ህትመት፣ በከተሞች ተነሳሽነት ተግባራዊ የተደረጉ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎችን በማሳየት፣ ጥናቶችን በማካፈል እና በማህበሩ አባላት መካከል የሃሳብ እና የልምድ ልውውጥን በማስተዋወቅ የሚያገለግል መደበኛ ህትመት መተግበሩ።
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ኩነቶች (VNG Events) በዋናነት እንደ ኮንፈረንሶች እና የኔትወርኪንግ መድረኮች የከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች እርስ በርስ እንዲገናኙ፣ እንዲተባበሩ እና እንዲማማሩ ጠቃሚ እድሎችን መፍጠሩ።
- በኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የሚዘጋጁ የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች አካታች እና ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው መቀረጻቸው፤ ይዘቶቻቸው እና አቀራረባቸው የተለያየ መጠን ካላቸው ከተሞች ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው።
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች የአባላት ግብረመልስን በማካተት መዘጋጀታቸው።

## 8. የአባል ከተሞች ተሳትፎ

የማህበሩ አባላት በተለያዩ የአመራርነት ተዋረድ ተሳታፊዎች ናቸው። በፖለቲካ ደረጃ ንቁ አባላት በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፣ በስራ አስፈፃሚ ቦርድ እና በተለያዩ ኔትወርኮች ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊዎች ናቸው። ሲቪል ሰርቫንቱ በልዩ ልዩ የስራ ቡድኖች፣ የኢንተርኔት ፎረሞች እና ለማህበሩ በባለሙያነት እና በአምባሳደርነት እንዲያገለግሉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሯል።

እነዚህን ስራዎች ለመደገፍ በ"አባልነት (1€ በአንድ ነዋሪ)" ስሌት ተሰልቶ በከተማው ጠቅላላ የህዝብ ብዛት ተባዝቶ አባል ከተሞች አመታዊ የአባልነት ክፍያ ይፈፅማሉ። በተጨማሪም "በአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ (3€ በአንድ ነዋሪ)" ተሰልቶ በከተማው ጠቅላላ የህዝብ ብዛት ተባዝቶ አባላት በፍላጎት ክፍያ ይፈጽማሉ።

በ"አባልነት (1€ በአንድ ነዋሪ)" እና በ"አስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ (3€ በአንድ ነዋሪ)" መካከል ያለው ቁልፍ ልዩነት፡-

"አባልነት (1€ በአንድ ነዋሪ)" (Membership Fee (1€ per inhabitant))

- በአንድ ነዋሪ 1€ የአባልነት ክፍያ ዘዴ ሁሉም አባል ከተሞች የማህበሩ አባል ሆኖ ለመቀጠል እና አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከፍሉት መሰረታዊ አመታዊ ክፍያ ነው።
- የአባልነት ክፍያው ለማህበሩ አጠቃላይ የስራ ማስኬጃ ጥቅም ላይ ይውላል።
- በመሰረታዊ አመታዊ የአባልነት ክፍያ ሁሉም አባላት የስልጠና ፕሮግራሞች፣ የልምድ ልውውጥ መድረኮች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ እና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል።

"የአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ (3€ በአንድ ነዋሪ)" Contribution Collective Implementation Mechanism (3€ per inhabitant):

- ይህ ከመሠረታዊ አመታዊ የአባልነት ክፍያ በተጨማሪ ከተሞች በፍቃደኝነት የሚከፍሉት መዋጮ ነው። ይሄንን ክፍያ እንደ አመታዊ መሰረታዊ ክፍያ አባላት እንዲከፍሉ አይገደዱም (optional)።
- ማህበሩ አመታዊ መዋጮን በመጠቀም ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ አባላት "3€ በአንድ ነዋሪ" ስሌት በከተሞቻቸው የህዝብ ብዛት ስሌት ተሰልቶ በፍላጎት በማዋጣት ልዩ የጋራ ስልጠና እና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን የሚያገኙበት አሰራር ነው።
- በዚህ ልዩ ስልጠና እና አውደጥናት ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት 3€ በአንድ ነዋሪ ስሌት ክፍያ የፈጸሙ ከተሞች ናቸው።

| ተ.ቁ | ባህሪ (Attribute) | "አባልነት (1€ በአንድ ነዋሪ)" የአባልነት ክፍያ | "የአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ (3€ በአንድ ነዋሪ)" ክፍያ |
|---|---|---|---|
| 1 | የክፍያ መጠን | 3€ በአንድ ነዋሪ | 3€ በአንድ ነዋሪ |
| 2 | የክፍያ ድግግሞሽ | መደበኛ አመታዊ የአባልነት ክፍያ ነው | በፈቃደኝነት የሚከፈል ወቅታዊ ክፍያ ነው |
| 3 | አስገዳጅነት | ለአባላት አስገዳጅ ክፍያ (mandatory) ነው | አባላት እንዲከፍሉ አይገደዱም (optional) (በፍላጎት የሚከፈል ክፍያ ነው) |
| 4 | ጠቀሜታ | የማህበሩን ዋና ተግባራትን እና አጠቃላይ የአባላትን ጥቅሞችን ይሸፍናል። | ልዩ በትብብር የሚከናወኑ የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ጥቅም ላይ ይውላል። |
| 5 | የአገልግሎቱ ተደራሽነት | ለሁሉም አባላት | ክፍያውን ለከፈሉ ከተሞች ብቻ |
| 6 | የበጀት ተፅዕኖ | ማህበሩ የተረጋጋ፣ ሊገመት የሚችል (predictability) የገቢ ፍሰት እንዲኖረው ያስችላል። | ማህበሩ የበለጠ ተለማጭ (flexibility) የሆነ ፈንድ ነው። |

***ሰንጠረዥ 1፡- የአባላት አመታዊ መዋጮ እና የአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ክፍያ ልዩነቶች ማጠቃለያ***

## የተገኙ ትምህርቶች

### ሀ/ ገቢን በተመለከተ

- አመታዊ የአባልነት ክፍያዎችን እና በአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ መዋጮ የማህበሩን ዘላቂ እና አስተማማኝ የገቢ አቅም መፍጠሩ።
- ከአባልነት የሚሰበሰበው ዓመታዊ መዋጮ ለማህበሩ ለስራ ማስኬጃ እና ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚውል ሲሆን በአስተዋጽዎ የጋራ ትግበራ የሚሰበሰብ መዋጮ ደግሞ ልዩ የስልጠና እና የልምድ ለውውጥ ፍላጎት ላላቸው ከተሞች ወጪ የሚሸፍን መሆኑ።
- የማህበሩ ገቢ ለአባልነት 1€ በአንድ ነዋሪ፣ የአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ 3€ በአንድ ነዋሪ ተግባራዊ መደረጉ የፋይናንስ መረጋጋትን መፍጠሩ።

### ለ/ የአባላት ተሳትፎ እና ባለቤትነትን በተመለከተ

- አባላት ለልዩ ስልጠናዎች እና ልምድ ልውውጥ መድረኮች ተጨማሪ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ማመቻቸት ተቀራርበው ለመስራት ፍላጎት ማሳየታቸው እና የባለቤትነት ስሜት መፍጠሩ።
- ይህ የማህበሩን የትኩረት መስኮች ከአባል ከተሞች ፍላጎቶች ጋር ለማጣጣም ይረዳል።

### ሐ/ አገልግሎቶችን በተመለከተ

- አባላት በሚከፍሉት ዓመታዊ ክፍያ ሁሉም አባላት መሰረታዊ አገልግሎቶችን ያገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ለጋራ ትግበራ አስተዋፅዖ አድራጊዎች የተሻሻሉ አገልግሎቶችን (ስልጠና፣ አውደጥናት ወዘተ) በመስጠት ያለባቸውን የአቅም ክፍተት ለመሙላት ያግዛል።

### መ/ ዕቅድና በጀትን በተመለከተ

- የተረጋጋ፣ ተደጋጋሚ የአባልነት ገቢ (recurring membership revenue) ለማህበሩ ጠንካራ የረጅም ጊዜ እቅድ እና በጀት ለማቀድ መሰረት መጣሉ።


- የአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ (3€ በአንድ ነዋሪ)" ክፍያ በአባል ከተሞች ፍላጎት መሰረት በልዩ ሁኔታ ለስልጠና እና ለልምድ ልውውጥ ወጪ በጀት በተለማጭነት መመደብ መቻሉ።

### ሠ/ በአባላት ተነሳሽነት የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን በተመለከተ

- አባላት በአስተዋጽኦ የጋራ ትግበራ ዘዴ (3€ በአንድ ነዋሪ)" የተከፈለን ክፍያ በጋራ እንዲጠቀሙበት ማመቻቸት ከተሞች የማህበሩን ስትራቴጂያዊ አጀንዳ እንዲተገብሩ ማስቻሉ።

## 9. ተቋማዊ አደረጃጀት

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ድርጅታዊ አወቃቀር ለከተሞች አገልግሎት ለመስጠት እና የጥብቅና ተልዕኮውን ለማሳካት በሚችል መልኩ የተደራጀ ነው። ማህበሩ የሁሉም ከተማ ከንቲባዎች የተወከሉበት ጠቅላላ ጉባዔ እና ስትራቴጂክ ጉዳዮችን ለመወሰን የስራ አስፈፃሚ ቦርድ አባላት አሉት። መቀመጫውን በሄግ ከተማ ያደረገው የማህበሩ ሴክሬታሪያት የእለት ከእለት ስራዎችን በማስተናገድ ለቦርድ እና ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ያደርጋል። ማህበሩ በተለያዩ የስራ ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን የስራ ክፍሎች ስያሜን በተመለከተ የህግ ጉዳዮች፣ የህዝብ ፖሊሲ እና የአባላት አገልግሎቶችን ያካትታል። (VNG, 2023)




***<u>ፎቶ 10፡- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ተቋማዊ አደረጃጀት</u>***

## የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ድርጅታዊ መዋቅር የሚከተሉትን ያካትታል፡-

### ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ (General Assembly)

ይህ ከሁሉም አባል ከተሞች የተዋቀረ ከፍተኛው ውሳኔ ሰጪ አካል ነው። ጠቅላላ ጉባዔው የካሪቢያን ኔዘርላንድስ በመባል የሚጠሩትን (ኩራካዎ፣ ሴንት ማርቲን፣ ቦኔየር፣ ሳባ እና ሴንት ኤውስታቲየስ) እና አሩባ ከተሞችን ያጠቃልላል። ጠቅላላ ጉባኤው አጠቃላይ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫን ያዘጋጃል፣ በጀት ያፀድቃል፣ የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላትን ይመርጣል። የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ይካሄዳል።

### ለ. የስራ አስፈጻሚ ቦርድ (Executive Board)

የቦርዱ ኃላፊነት የማህበሩን አጠቃላይ ስትራቴጂያዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲሁም የፖሊሲ እና አድቮኬሲ የስራ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል። የአባል ከተሞችን የተለያዩ አመለካከቶችን የሚወክሉ ከንቲባዎች እና የምክር ቤት አባላትን ያቀፈ ነው።

የስራ አስፈጻሚ ቦርድ

- የኮሚቴ ሰብሳቢዎች የቦርድ አባላት ናቸው።
- የቦርዱ አባላት ቁጥር በኮሚቴ ሰብሳቢዎች ብዛት ይወሰናል።
- ቦርዱ በዓመት 11 ጊዜ የሚሰበሰብ ሲሆን ከንቲባዎች፣ ምክትል ከንቲባዎች፣ የምክር ቤት አባላት፣ የከንቲባ ጽ/ቤት ሃላፊዎችና የማዘጋጃቤት ሠራአሥኪያጆችን ያቀፈ ነው።
- ቦርዱ አመታዊ አጀንዳዎችን፣ አመታዊ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል።
- ከማህበሩ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥ እና 12 ሌሎች የተመረጡ የቦርድ አባላትን ያቀፈ ነው።
- የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ለ4 ዓመታት የሚያገለግሉ ሲሆን በምርጫ እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ።
- የስራ አስፈፃሚ ቦርድ ስብሰባ ቃለጉባዔዎች ለጠቅላላ ጉባኤ አባላት እንዲያውቁት በሶፍት ኮፒ ይሰጣቸዋል።




***ፎቶ 11፡- የኡተረክት ከተማ ከንቲባ እና የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የወቅቱ የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ሰብሳቢ***

## ሐ. የፖሊሲ ኮሜቴዎች (Policy Committees)

- በፖሊሲ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተዋቀሩ 9 ኮሚቴዎችን እና 2 ኮሌጆችን ያካትታል፡፡
- ስብጥሩ ከንቲባዎችን፣ ምክትል ከንቲባዎችን፣ የምክር ቤት አባላትን፣ የከንቲባ ጽ/ቤት ሃላፊዎችን እና የማዘጋጃ ቤት ሥራ አሥኪያጆችን ያካትታል፡፡
- እውቀት፣ ኔትወርክ እና የስራ ልምድ አስፈላጊ የመምረጫ መስፈርቶች ናቸው፡፡

## መ. ሴክሬታሪያት

በሴክረታሪ ጀነራል የሚመራ፣ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ቦርድ የሆነ፣ የተቋሙን እለት ተእለት ስራዎችን የሚመራና የሚተገብር መዋቅራዊ አደረጃጀት ነው፡፡ የሴክሬታሪያቱ ዋና ዋና ተግባራት የእውቀት መጋራት መድረኮችን ማመቻቸት፣ ለከተሞች ጥብቅና መቆም እና አገልግሎት መስጠት (knowledge sharing, advocacy, and service provision) ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስቱ ምሰሶዎች የማህበሩ መሠረት ናቸው፡፡ (VNG, 2024) ማህበሩ ከሚሰራቸው ሦስቱ ዋና ዋና ተግባራት እና ሌሎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡-

### i. ጥብቅና እና ከተሞችን የመወከል ሚና (Advocacy and Representative Role)

ሁሉም የኔዘርላንድ ከተሞች ጥቅሞቻቸውን በአገር እና በአውሮፓ ደረጃ በመወከል የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር እንደ ዋና ተሟጋች ድርጅት ሆኖ ይሰራል። ማህበሩ ከተሞችን በሚነኩ የፖሊሲ ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፤ የከተሞች ጉዳይ በፖለቲካዊ ውይይቶች መደመጣቸውን ያረጋግጣል። (VNG, 2024)

### ii. የእውቀት መጋራት እና የአቅም ግንባታ (Knowledge Sharing and Capacity Building)

በከተሞች መካከል የእውቀት እና የልምድ መጋራትን ማመቻቸት የማህበሩ ቁልፍ ኃላፊነት ነው። ተቋሙ ለከተሞች ሞዴል ማንዋሎችን በማዘጋጀት፣ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ከተሞች የተሻሉ ተሞክሮዎችን እና አዳዲስ እውቀቶች እና አሰራሮችን እንዲለዋወጡ ያደርጋል። "The Hague Academy for Local Governance" ስልጠናዎችን በተለያዩ አገራት ለሚገኙ ከተሞች የሚሰጥ ሲሆን ለኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ደግሞ ማህበሩ ያመቻቻል። (VNG, 2024)

### iii. የአገልግሎት አቅርቦት

ማህበሩ ከተሞች በህግ የተሰጣቸውን ተግባራት ለመፈፀም የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው። ይህም በተለያዩ የማህበረሰብ ተግዳሮቶች ላይ የምክር አገልግሎትን፣ የተሻሉ ተሞክሮዎች በከተሞች ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ እና ውጤታማ የከተሞች አስተዳደር ማዕቀፍ ተግባራዊ ማድረግን ያካትታል። (VNG International, 2024)

### iv. ለዲጂታላይዜሽን እና ለስማርት ሲቲ ስራዎች ድጋፍ

ማህበሩ ከተሞችን ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እና ለስማርት ሲቲ ጥረቶቻቸው ድጋፍ ያደርጋል። ድጋፎቹም የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ለማሻሻል ዲጂታል መሳሪያዎችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል በስልጠና እና የግብዓት አቅርቦት ያካትታል። (VNG, 2024)

## v. በአለም አቀፍ ደረጃ ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ

ማህበሩ በአለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲው (VNG International) በአለም አቀፍ ደረጃ የከተሞችን አቅም ያሳድጋል፡፡ ይህ በተለያዩ ሀገራት በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ ያሉትን የስልጠና ፕሮግራሞችን እና ድጋፎችን ያካትታል፡፡ (VNG International, 2024)

## vi. ለከተማ ነክ ጉዳዮች አጀንዳ መቅረጽ

ማህበሩ ከተሞች አግባብነት ያላቸውን አካባቢያዊ ጉዳዮችን እና ተግዳሮቶችን በጋራ እንዲፈቱ ያስችላቸዋል፡፡ ማህበሩ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ከተሞች ለጋራ ራዕይ በብቃት እንዲሰሩ ያግዛል፡፡ (VNG, 2024)

## vii. የትብብር መረቦችን መገንባት (Building Collaborative Networks)

ማህበሩ በከተሞች መካከል የትብብር መድረክን በመፍጠር ሽርክናዎችን እና አውታረ መረቦችን (partnerships and networks) በማፍራት የሀብት መጋራትን እና የጋራ ተግባርን ያጎለብታል፡፡ ይህ ህዝብን የሚጠቅሙ ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ (VNG, 2024)

## የተገኙ ትምህርቶች

- ጠቅላላ ጉባዔው ሁሉንም ዓባል ከተሞች ያቀፈ ዴሞክራሲያዊና ሁሉን አቀፍ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መርህን የተከተለ መሆኑ በአባል ከተሞች መካከል ጠንካራ የባለቤትነት ስሜት እና ተሳትፎን ማጎልበት አስችሏል፡፡
- ከአባል ከተማ ከንቲባዎች የተውጣጡ ብዝሃነትን እና ውክልናን መሰረት ያደረገ የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ማዋቀር ሚዛናዊ አመራር (Balanced Leadership) ለመፍጠር አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው፡፡
- የአባል ከተሞችን የቴክኒክ እውቀት ለመጠቀም ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን እና የስራ ቡድኖችን ማዋቀር ቁልፍ በሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ከተሞች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡
- የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ተቋማዊ አደረጃጀቱ ተዋረዱን የጠበቀ፣ ግልጽ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚከተል፣ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር መላመድ የሚችል እና ለአባል ከተሞች ፍላጐት ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ አስችሎታል፡፡ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በተመሳሳይነት

በራሱ ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ተለማጭነት፣ ከተለዋዋጭ አገራዊ ሁኔታዎች ጋር ራሱን ማላመድ እና ለከተሞች ፈጣን ምላሽ ሰጪነት ማካተት እና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 10. አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG- International)

ማህበሩ አለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲ (International Cooperation Agency (VNG International)) ያለው ሲሆን ከተሞችን እና የአካባቢ መንግስታትን በአለም አቀፍ ደረጃ በማጠናከር ከ40 በላይ ሀገራት እየሰራ ይገኛል፡፡ አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG International) በአለም አቀፍ ደረጃ ባልተማከለ አስተዳደርና በአቅም ግንባታ ላይ ያተኮሩ ከ60 በላይ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ ተቋሙ የኔዘርላንድ ከተሞች ተሞክሮዎችን ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመለዋወጥ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የአለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ሌላው ቁልፍ ተግባሩ በአለም አቀፍ ደረጃ ዲሞክራሲያዊ የአካባቢ አስተዳደርን ማጠናከር ነው፡፡ የሄግ አካዳሚ ፎር ሎካል ገቨርናንስ (The Hague Academy for Local Governance) በኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ተነሳሽነት የተቋቋመ ሲሆን በአለም ዙሪያ ላሉ የከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች የስልጠና እና የትምህርት ፕሮግራሞችን ይሰጣል፡፡

### የተገኙ ትምህርቶች

- አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (ቪኤንጂ ኢንተርናሽናል) በያልተማከለ አስተዳደር፣ በፋይናንስ አስተዳደር እና በአገልግሎት አሰጣጥ ባሉ ዘርፎች ለትብብር መድረኩ እና ለአባል ከተሞች ጠቃሚ ልምድ ስላላቸው ከተቋሙ ጋር የተጀመረው ተባብሮ የመስራት ልምድ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለብን ትምህርት ተወስዷል፡፡
- አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የመሰረታቸው አለምአቀፍ ኔትወርኮች እና አጋርነቶች በኔዘርላንድ እና በኢትዮጵያ የእውቀት እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ እንደሚያስችል ትምህርት ተወስዷል፡፡
- ትብብር መድረኩ ከአለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አለም አቀፍ ትብብር አካሄድ ትምህርት ተወስዷል፡፡
- አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ከተሞችን የማጠናከር ስራው ከትብብር መድረኩ ተልዕኮ ጋር የተጣጣመ መሆኑ እና በቀጣይም በጋራ ለመስራት ትምህርቶች ተወስዷል፡፡
- አለም አቀፉ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የፕሮጀክት እና የፕሮግራም ማኔጅመንት ልምድ ትብብር መድረኩ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በትብብር ፕሮጀክቶች እንዴት እንደሚቀረጽ እና እንደሚተገበር ትምህርት ተወስዷል፡፡

## 11. የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር በፖሊሲ አወጣጥ ሂደቶች ውስጥ ባለድርሻ አካላትን በዋናነት የመንግስት ተቋማትን፣ የግል ድርጅቶችን፣ ዜጎችን እና ከተሞችን ያሳትፋል። (FMO, n.d.) ይህ አካታች አካሄድ ግልጽነትን እና ትብብርን በማጎልበት የተለያዩ እሳቤዎችን እና አመለካከቶችን በግብዓትነት በመጠቀም አካባቢያዊ ችግሮችን የሚፈቱ ውሳኔዎችን እንዲቀርጹ ያስችላቸዋል። (Tandfonline, 2020) ማህበሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት የሚመራበት ሞዴል "Poldermodel" ተብሎ ይጠራል። ፖልደርሞዴል የኔዘርላንድን የመተባበር እና የጋራ መግባባት የመፍጠር ባህልን የሚያንፀባርቅ፤ ለውሳኔ አሰጣጥ እና ችግር አፈታት ፍቱን ዘዴ ነው። ፖልደርሞዴል በአገሪቱ በታሪክ ከውሃ አያያዝ እና ከመሬት መልሶ ማልማት ችግሮች አፈታት ጋር ተግባራዊ ሲደረግ የነበረ ስኬታማ ስልት ነው። ይህን ሞዴል በመጠቀም ለበርካታ አመታት የኔዘርላንድ ከተሞች የጋራ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ችለዋል።

**የሞዴሉ ዋና መርህ** ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በጋራ መግባባት መስራትን ያጠቃልላል። (OCED, 2023) ይህ ሞዴል ባለድርሻ አካላት የጋራ ግቦችን ለማሳካት በትብብር እንዲሠሩ እና የጋራ ኃላፊነት እንዲኖራቸው ያበረታታል። **የፖልደርሞዴል ዋና ዓላማ** ከመንግስት ተቋማት እና ከሲቪል ማህበራት የተለያዩ ፍላጎቶችን በማቀናጀት ለፖሊሲዎች በርካታ ግብዓቶችን በማሰባሰብ የፖለቲካ መረጋጋትን እና ውጤታማነትን ማጎልበት ነው። (Tandfonline, 2020)

ፖልደርሞዴል በሚመለከታቸው አካላት መካከል የተለያዩ አስተያየቶች ቢኖሩም ትብብር ቅድሚያ የሚሰጥበት የጋራ ስምምነት ውሳኔ አሰጣጥ ዘዴ ነው። ችግሮችን በውይይት ለመፍታት እንደ ማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል፣ እያንዳንዱ አካል በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ውስጥ እኩል ድምጽ እንዲኖረው ያስችላል። (Wikipedia, 2024) **የፖልደርሞዴል ባህሪያት** ለብዝሃነት እውቅና መስጠት እና ከአፍራሽ አመለካከት ይልቅ በትብብር ላይ ማተኮርን ያካትታሉ። (Economist, 2002) በኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የሚዘጋጁ ስብሰባዎች ድግግሞሽ በፕሮጀክት ውስብስብነት እና በባለድርሻ አካላት ፍላጎት መሠረት ይለያያል። (VNG International, n.d.)

በኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ውስጥ ያለው ፖልደርሞዴል ከተለያዩ ከተሞች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላትን በማሰባሰብ የጋራ ጉዳዮችን ለመለየት እና ሁሉንም የሚጠቅሙ መፍትሄዎችን ለመፍጠር ነው። ትዕግስትን፣ አካታችነትን እና ተግባራዊነትን ዋጋ የሚሰጥ ሂደት ነው። (It's a process that values patience, inclusivity, and pragmatism)

ፖልደርሞዴል ሰዎች ለማሸነፍ ከሚታገሉባቸው ዘዴዎች የተለየ ነው። አንዱ ወገን ሁሉንም ነገር እንዲያሸንፍ፣ ሌላኛው ወገን እንዲሸነፍ ከማድረግ ይልቅ ሁሉንም ሰው በተወሰነ ደረጃ የሚያስደስት መፍትሄ ለማግኘት ያስችላል። ማህበሩ ብዙ ከተሞችን የሚነካ ውስብስብ ጉዳይ ሲያጋጥመው ዝም ብሎ ውሳኔ አይወስንም ወይም ትላልቅ ከተሞች በአነስተኛ ከተሞች አስተያየት የበላይ እንዲሆኑ አይፈቅድም። ይልቁንም ጥንቃቄ የተሞላበት የምክክር ሂደት ይጀምራል። የተለያየ መጠን ያላቸው ከተሞች ተወካዮች በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲወያዩ መድረክ ያመቻቻል።

## 12. የኔዘርላንድ የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር (BZK) እና የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የስራ ግንኙነት

የኔዘርላንድ የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር የከተማ ልማት ነክ እና ያለተማከለ አስተዳደር ጉዳዮችን በኔዘርላንድ አገር የሚመራ የፌደራል ተቋም ነው። የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር የከተሞችን አቅም እና ውጤታማነት ለማሳደግ ለኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የተለያዩ ድጋፎችን ይሰጣል። ይህ ድጋፍ የፋይናንስ ድጋፍን፣ የትብብር ስራዎችን፣ ያልተማከለ አስተዳደርን ለማስፋፋት፣ የአቅም ግንባታ፣ ለማዘጋጃ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ድጋፍን ያጠቃልላል። (VNG, 2024)

### ሀ/ የፋይናንስ ድጋፍ

የኔዘርላንድ የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር በተለይ በካሪቢያን አካባቢ የኔዘርላንድ ከተሞች የትብብር መድረክ የሚተገብራቸውን ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን በፋይናንስ በመደገፍ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቦናይር፣ ሲንት ዩስታቲየስ እና ሳባ ያሉ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር ዓላማ ያለውን ፕሮጀክት በፋይናንስ በመደገፍ በእነዚህ ማዘጋጃ ቤቶች ለሚገጥሟቸው ከአስተዳደርና ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ እገዛን ይሰጣል። (VNG Caribbean Desk set to launch on July 1, 2024)

### ለ/ የአቅም ግንባታ ስራዎች

የኔዘርላንድ የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር ከኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ጋር በመተባበር የከተሞችን ችግር በመሰረታዊነት በሚፈቱ ልዩ የአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ይሰራል።

ይህም የእውቀት መጋራትን እና የከተማ አስተዳደርን አቅም ለማጎልበት የሚያስችል እውቀትና ግብአት ማቅረብን ይጨምራል። (VNG International, 2024)

## ሐ/ የትብብር ፕሮግራሞች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ማህበሩ የካሪቢያን ክልል ከተሞችን የአቅም ክፍተቶች መነሻ በማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለመደገፍ የካሪቢያን ክልል ከተሞች የድጋፍ ፕሮጀክት ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል። ይህ የትብብር ፕሮግራም ሀገራዊ ፖሊሲዎች እና ማዕቀፎችን ታሳቢ በማድረግ በከተሞች እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እየተሰራ ይገኛል። (VNG and BZK launch new Caribbean support program, 2024).


## መ/ የፖሊሲ ልማት ድጋፍ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ባለሙያዎችን በከተማ አስተዳደር በተለይም በልማት ትብብር እና በፖሊሲ ቀረጻ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርግ ግብዣ ያደርጋል። ይህ ተባብሮ የመስራት ልምድ የከተሞች ፍላጎቶች በአገራዊ ፖሊሲዎች ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ የበለጠ ምላሽ ሰጪ የአስተዳደር ማዕቀፍ እንዲኖር ያስችላል። (Priority Actions - Digital Government, 2024)

## ሠ/ የፕሮጀክት ፋይናንስ

አብዛኛዎቹ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር አለምአቀፍ ፕሮጀክቶች ከፊል ፋይናንስ የሚደረጉት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ነው። የኔዘርላንድ የአገር ውስጥ እና የመንግስት ጉዳዮች ሚኒስቴር ከሌሎች ተቋማዊ አጋሮች በዋናነት ከአውሮፓ ህብረት እና ከአለም ባንክ ጋር በመሆን የፕሮጀክት ፋይናንስ ድጋፍ ያደርጋል። ይህ ዘርፈ ብዙ የፋይናንሺያል ድጋፍ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥን በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደግፉ የተለያዩ ስራዎችን እንዲሰራ ያስችለዋል። (VNG's international project, n.d.) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለማህበሩ የሚሰጠው ድጋፍ በዋናነት የፋይናንስ ድጋፍ፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች ድጋፍ፣ የትብብር መርሃ ግብሮች፣ የፖሊሲ ልማት ድጋፍ እና የፕሮጀክት ፋይናንሲንግ ለማህበሩ ውጤታማነት እና አይበገሬነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል። (Ministry VSA and VNG, 2024)

## አባሪ 1፡ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር ታሪክ በቻርት



# ማጣቀሻዎች

About the VNG (2024). Retrieved from [https://vng.nl/artikelen/about-the-vng] (https://vng.nl/artikelen/about-the-vng)

Association of Dutch Municipalities (Vereniging van Nederlandse Gemeenten) (2024). Retrieved from (https://living in.eu/smartcommunities/association-dutch-municipalities-vereniging-van-nederlandse-gemeenten-vng)

Association of Netherlands Municipalities (2023). *About the VNG*. Available at: https://vng.nl/artikelen/about-the-vng [Accessed 3 Oct. 2024].

CoR (n.d.). Netherlands intro. (https://portal.cor.europa.eu/divisionpowers/Pages/Netherlands-intro.aspx)

Economist (2002) Model makers. Available at: https://www.economist.com/special-report/2002/05/04/model-makers

International Cooperation Agency of the Association of Netherlands Municipalities (2024). Retrieved from (https://platforma-dev.eu/partner/association-of-netherlands-municipalities/)

Jeroense, P. (2024). "The Dutch Association of Municipalities" Presentation to Ethiopian Cities Association Delegation.

Ministry of the Interior and Kingdom Relations (2022). Decentralization in the Netherlands. Retrieved from (https://www.rijksoverheid.nl/onderwerpen/decentralisatie)

Ministry VSA and VNG (2024). Retrieved from (http://smn-news.com/index.php/st-maarten-st-martin-news/29279-ministry-vsa-and-vng-host-mediation-congress-friday-on-june-1st.html)

Netherlands | The Global State of Democracy - International IDEA. (https://www.idea.int/democracytracker/country/netherlands)

OECD (2023). The Netherlands' multi-stakeholder sectoral agreements promote Responsible Business Conduct. https://www.oecd.org/en/publications/development-co-operation-tips-tools-insights-practices_be69e0cf-en/the-netherlands-multi-

stakeholder-sectoral-agreements-promote-responsible-business-conduct_25ba114b-en.html)

Priority 2.6 Actions - Digital Government (2024). Retrieved from (https://www.nldigitalgovernment.nl/overview/digitalisation-policy/value-driven-digitalisation-work-agenda/2-everyone-will-be-able-to-trust-in-the-digital-world/2-6-implementation-of-national-and-eu-regulations-compliance-and-monitoring/priority-2-6-actions/)

Statista. (2023). Urban Population in the Netherlands 2023. Retrieved from [Statista website] (https://www.statista.com).

Statista. (2024). Netherlands: Degree of urbanization from 2013 to 2023. Available at: https://www.statista.com/statistics/276724/urbanization-in-the-netherlands/ (Accessed: 3 October 2024).

Tandfonline (2020). Quiet acceptance vs. the 'polder model': stakeholder involvement in.... (https://www.tandfonline.com/doi/full/10.1080/09654313.2020.1735310)

Tandfonline (2018). The case of the Dutch decentralized unitary state. (https://www.tandfonline.com/doi/full/10.1080/13597566.2018.1502179).

The Hague Academy for Local Governance, n.d. Available at: https://thehagueacademy.com/

The Hague Academy for Local Governance (n.d.). *Training Courses*. Available at: https://thehagueacademy.com/course/ [Accessed 3 Oct. 2024].

VLEX (2018). Local Government in the Netherlands - Local government in the member states of the European Union: a comparative legal perspective. (https://eu.vlex.com/vid/local-government-in-the-netherlands-394138962).

VNG (2023). About VNG. Retrieved from (https://vng.nl)

VNG International (2023). VNG International. Retrieved from (https://vng-international.nl)

VNG Caribbean Desk set to launch on July 1 (2024). Retrieved from (https://www.thedailyherald.sx/islands/vng-caribbean-desk-set-to-launch-on-july-1)

VNG International (2024). Retrieved from (https://www.vng-international.nl/taxonomy/term/85)

VNG and BZK launch new Caribbean support program (2024). Retrieved from (https://www.curacaochronicle.com/post/main/vng-and-bzk-launch-new-caribbean-support-program/)

VNG (Association of Dutch Municipalities) – Smart Documents (2024). Retrieved from (https://smartdocuments.com/partners/vng/)

VNG International The Hague (2024). Retrieved from [https://www.vng-international.nl/about-us/vng-international-the-hague](https://www.vng-international.nl/about-us/vng-international-the-hague)

VNG International (2017). Local Government in the Netherlands. (https://www.vng-international.nl/wp-content/uploads/2017/12/Local-Government_in-the-Netherlands.pdf).

VNG International (n.d.). *Local Government in the Netherlands*. Available at: https://www.vng-international.nl/wp-content/uploads/2017/12/Local-Government_in-the-Netherlands.pdf [Accessed 3 Oct. 2024].

VNG International (n.d.). *Global Commitment, International Cooperation, Local Action*. Available at: https://vng.nl/sites/default/files/2020-04/handreiking_-_global_commitment_international_cooperation_local_action._an_aid_for_local_governments.pdf [Accessed 3 Oct. 2024].

VNG (2017). About the VNG. Available at: https://vng.nl/artikelen/about-the-vng [Accessed 3 Oct. 2024].

VNG International (2023). You can now watch the Webinar on digital citizen surveys. Available at: https://www.vng-international.nl/you-can-now-watch-webinar-digital-citizen-surveys [Accessed 3 Oct. 2024].

VNG International (2023) VNG International. Available at: https://www.vng-international.nl/about-us/vng-international-the-hague (Accessed: 3 October 2024).

VNG (2023) About the VNG. Available at: https://vng.nl/artikelen/about-the-vng (Accessed: 3 October 2024).

VNG International (2022). *Voluntary Subnational Review*. Available at: https://www.gold.uclg.org/sites/default/files/field-document/the_netherlands_2022_vsr_eng.pdf [Accessed 3 Oct. 2024].

VNG Magazine (2024). *VNG Magazine*. Available at: https://vng.nl/rubrieken/vng-magazine [Accessed 3 Oct. 2024].

VNG International (2022). *Upcoming events*. Available at: https://www.vng-international.nl/upcoming-events [Accessed 3 Oct. 2024].

Wikipedia (2024) Polder model. Available at: https://en.wikipedia.org/wiki/Polder_model